የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY
☎ 55 35 06, 55 17 89, 12 39 00 - Fax 251-1-55 31 55 - ✉ 882
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ - Addis Ababa, Ethiopia

ቁጥር Ref. No. መለ/3/804/02
ቀን Date 9/11/02

## ከሰኔ 01 እስከ 24 ቀን 2002 ዓ.ም በመኢአድ አባላት ላይ በየአካባቢው የተፈፀሙ ከፍተኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሥነ-ምግባር ጥሰቶች

መኢአድ በምርጫ ቦርድና በገዢው ፓርቲ የጋራ ስልታዊ አሠራር ምርጫው ፍትሐዊ፣ ነፃና በህዝብ ታዓማኒነት ያጣ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ገዢው ፓርቲ እና መንግሥት ይህም አልበቃ ብሎት በአሁኑ ግዜ ደግሞ ሰሜን ጎንደር ዞን በጃናሞራ፣ በደባርቅ፣ በዳባት፣ በወገራ፣ በበለሳ፣ በጭልጋ፣ በደንቢያ፣ በጎንደር ዙሪያ፣ በአለፋ፣ ጠቁሳ፣ ወዘተ በርካታ ታዛቢዎቻችንና አባሎቻችን እንግልት፣ መታሰር፣ መደብደብ፣ መሬትና የመሬት ባለቤትነት ደብተር ነጠቃ እንዲሁም ልዩ ልዩ ግፎች እየተፈፀመባቸው ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

1. በጎንደር ዙሪያ ወረዳ ደንቀዝ ጎመንጌ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ተቀባ ሞላና አቶ ተሰፌ ሞላ የመኢአድ አባል በመሆናቸው ብቻ በፈጠራ ክስ ፍ/ቤት ቀርበው እያንዳንዳቸው ብር 300 ተቀጥተዋል፡፡

2. አቶ እዘዘው መኳንንት በበለሳ ወረዳ በገላ ሮቢት ከተማ ነዋሪ፣ የመኢአድ አባልና ታዛቢ ከግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም ምርጫ በኋላ የደረሱበት አልታወቀም፡፡ እንዲሁም ሌሎች የምርጫ ታዛቢዎች ተደብድበዋል፣ ማስፈራራት እና እንግልት ደርሶባቸዋል፡፡

3. አቶ ሙሉጌታ ዳኜ፣ ኤፈሶን ምርጫ ክልል፣ ሣር ምድር ምርጫ ጣቢያ በመዝገብ ቁጥር 2 ገፅ 3 ተ.ቁ 45 ላይ ተመዝግበው ለመምረጥ ሲሄዱ መምረጥ አይፈቀድልዎትም፣ ታዛቢዎችን በመኖሪያ ቤትዎ አሳድረዋል በማለት ድብደባና እሥራት ደርሶባቸዋል፡፡ የመሬት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተወስዶባቸዋል፤ በሕገ-መንግሥቱ የተሰጠው የመምረጥ መብታቸውም ተገፎአል፡፡

4. አቶ ፀጋዬ ታረቀኝ ከልካይ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ሊቦ ከምከሞ ወረዳ ምርጫ ክልል፣ በ1999 ዓ.ም ጥር 22 ክስ ተመስርቶባቸው አራት ዓመት ከ6 ወር ሲመላለሱ ከቆዩ በኋላ ምርጫው ከመድረሱ በፊት በጥድፊያ ሚያዝያ 26 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ 6 ስዓት በአንድ ምስክር፣ ዐቃቤ ህግ ማስረጃ ሳያሟላ፣ 4 ዓመት ተፈርዶባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ አቶ ፀጋዬ በ2002 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ የተወካዮች ም/ቤት እጩ ተወዳዳሪ በመሆናቸው ሳይታሰሩ ቢቀሩም ከምርጫው በኋላ እንደሚታሰሩ ስለተነገራቸው ከቀያቸው ሸሽተው በስደት ላይ ይገኛሉ፡፡ አቶ ፀጋዬ ወላጅ እናት የሌላቸው ህፃናትን ጨምሮ የ8 ቤተሰብ አስተዳዳሪ ናቸው፡፡